# ማጠቃለያ ስለ RIB ፕሮጀክት

ይህ ማጠቃለያ በተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ይገኛል። የተቀረው የዌፕ ሳይቱ/ድረገጽ ይዞታ ግን አልተተረጎመም፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ እንግሊዝ አገር ስኬታማ የሆነ ንግድ ለመጀመር ከፈለጉ የእንግሊዘኛ ቋንቋ በደምብ ማወቅ ኣስፈላጊ ስለሆነ ነው።

**ለምን ‘ስደተኞትን ወደ ንግድ’?**

ምክንያቱም ስደተኞች ከሌሎች ስደተኛ ያልሆኑ ሰዎች ሲወዳደሩ ስራ ለመቀጠር እስከ ስድስት ግዜ ያህል አነስተኛ እድል ስላላቸው። ይህ ደግሞ የስደተኞች እውቀትና ችሎታ በከንቱ ማባከን ነው። ስለሆነ ይህ የንግድ መጀመር ወይም ማህበራዊ ድርጅቶች ማስጀመር ሌላ መፍትሔ ነው።

**እንዲሁ ቀላል ቢሆን ኖሮ!**

ልክ እንደ ሌሎች እድል የማይሰጣቸው ሰዎች፡ አዲስ ንግድ ለመጀመር የሚፈልጉ ስደተኞች የተለያዩ መሰናክሎች ያጋጥማቸዋል። ለምሳሌ፡ ታዋቂነት ያላገኘ የስራ ልምድ፣ የገንዘብ ብድር ለማግኘት እድል፣ ቋንቋ፣ መረጃ የማግኘት እድል፣ ዘረኝነት፣ ያላቸው ስልጣን አለመታመንና የእንግሊዝ አገር የስራ ባህል አለማወቅ የመሳሰሉትን መሰናክሎች ሊጠቀሱ ይችላሉ።

የኮሚኒቲው የስደተኞች ማህበሮች መሰረታዊ የሆነ የንግድ መጀመር ምክር ለማቅረብ ብቃት ስሌላቸው፡ እንዲሁም የሚያቀቧቸው ዋና አማካሪዎች ደግሞ ስላሉት መሰናክሎችና መደበኛ የሆነ እርዳታ እንዴት ለማቅረብ እንደሚችሉ አያውቁም።

ስለሆነ ስድተኞችን ወደ ንግድ ማስጀመር የሚባለው ፕሮግራም እነዚህ ችግሮችን ለመፍታት የተቋቋመ ነው። ዋና ዓላማው ደግሞ፤

***ንግድ ለመጀመር የሚፈልጉት ስደትኞችን ባሉት ድጋፎች በመጠቀም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ እርዳታ ለማቅረብ ነው።***

**የስደተኞችን ወደ ንግድ ዌፕ ሳይት/ድረ ገጽ**
ይህ ዌፕ ሳይት/ድረ ገጽ ስለ ፕሮጀክቱ መረጃዎች እንደ ምክር፡ ጥናቶች፡ መመርያዎችና ስላሉት የመማርያና መሳርያዎችና የስልጠና እርዳዎች ያቀርባል።

**ንግዱን ለመጀመር በራስህ መወሰን የሚያስችሉ እርዳታዎች**
ይህ መጀመር የሚያስቡትን ንግድ ለእርስዎ ይሆናል አይሆንም ለመወሰንና ንግዱን ለመጀመር እርዳታ ለማቅረብ ይረዳል።

**ለዋና አማካሪዎች የሚሆን የመማርያ መሳርያዎች**
ይህ ስለ ስደተኞች ጉዳዮችና ስደተኞች ንግድ ለመጀመር በሚያስቡበት ጊዜ ምን ዓይነት የንግድ ምክር እንደሚያስፈጋቸው ለመርዳት ነው።

**ለስደተኛ ማህበሮች የሚሆን የመማርያ መሳርያዎች**
ይህ መሰረታዊ የንግድ አማካሪዎች ፈልጎ በማግኘትና ከነሱ ጋርም አብሮ በመስራት መሰረታዊ የሆኑ የንግድ ምክሮችና እርዳታዎች ያቀርባል።

**የስልጠና ትምህርቶች**
ይህ ፕሮጀክት ንግድ መክፈት ለሚፈልጉ ስደተኞች የሚሆን መሰረታዊ የንግድ ምክሮች፡ ስደተኞች ማነቃቃትና የንግድ መጀመር ስልጠናዎች ያቀርባል።

ይህ ዌፕሳይት/ድረገጽ ጠቃሚ ሆኖ እንደሚያገኙት ተስፋ እናደርጋለን። ማንኛውም ዓይነት አስተያየት ካልዎት እባክዎትን ያነጋግሩን።

© The Prince’s Trust and the Refugee Council 2006 